በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና አዛኝ በሆነው እንጀምራለን

ህዳር 17-2004 ዓ.ል 

ለክቡር አቶ መለስ ዜናዊ

ጠቅላይ ሚኒስትር

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

አዲስ አበባ

ኢትዮጵያ

*ጉዳዩ፡- የኢትዮጵያን ሙስሊሞች ወቅታዊ ችግር ይመለከታል*

ይህ ደብዳቤ በጅዳ ጣኢፍ መካ እና መዲና አካባቢ ነዋሪ ከሆኑት ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ተዘጋጅቶ ጅዳ በሚገኘው የኢትዮጵያ ኢምባሲ በኩል ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት እንዲቀርብ የተላከ ነው።

እንደሚታወቀው ሐገራችን ኢትዮጵያ ለእድገቷ ጸር ከሆኑ ጨቋኝ ስርዓቶች በህዝቦች ያላሰለሰ ትግል ተላቅቃ እነሆ በእድገት እና ትራንስፎርሜሽን ጎዳና ፈጣን ለውጥ እያስመዘገበች ትገኛለች።

በአካባቢያችን ነዋሪ የሆነው ሙስሊም ህብረተሰብ ለፕሮግራሙ መሳካት ከመንግስት ጎን በመሆን የልማት አጋርነታችንን በማሳደግ ድህነትን ታሪክ ለማድረግ ቆርጠን ተነስተናል።

የኢህአዴግ መንግስት ስልጣን ከተረከበበት ጊዜ ጀምሮ ለኢትዮጵያ እድገት እና ብልጽግና ታሪክ የማይረሳቸው የልማት ስራዎችን አከናውኗል ብንል ማጋነን አይሆንም።

በፌዴራላዊ የአወቃቀር ስርዓት ሁሉም ብሄር ብሄረሰብ ባህሉን እምነቱን ቋንቋውን እና ታሪኩን ጠብቆ ክልሉን እንዲያለማ መንግስት በፈጠረው ምቹ አጋጣሚ መጠነ ሰፊ የልማት ስራዎች የተሰሩ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ በሃገሪቱ የትምህርት ሽፋን እንዲያድግ ዘመናዊ ታላላቅ ዩኒቨርስቲዎችና የትምህርት ተቋማትን በመገንባት፣ በዘርፉ የተሰማሩ ባለሐብቶችን በማጠናከር ከገጠር እስከ ከተማ ሁሉም በአቅራቢያው ጥራት ያለው ትምህርት እንዲያገኝ በማድረግ በኩል አመርቂ ውጤት ተኮር ስራ ተሰርቷል። በኢንዱስትሪውም በኩል ከታላላቅ ሃይል ማመንጫዎች እና ፋብሪካዎች በተጨማሪ ዘመናዊ የመስኖ እርሻን በማስፋፋት የአርሶ አደሩን ህይወት ለመለወጥ ተችሏል። ዘመናዊ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ግንባታም ከመዲናችን አዲስ አበባ አልፎ በየክልሎችም የህብረተሰቡን ችግር ከመፍታት አልፈው ለከተማዎች ውበት ሆነዋል። ሃገራችን ከዘመኑ ቴክኖሎጂ ጋር እንድትራመድ ዓለም አቀፍ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ የኢንተርኔት ገመድ መዘርጋቱ ጋር የሞባይል እና የስልክ እንዲሁም የመብራት እና የንጹህ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ከመሆኑም በተጨማሪ ተመሳሳይ የልማት ስራዎች በስፋት ከገጠር እስከ ከተማ ለህብረተሰቡ ከማዳረስ ጎን ለጎን የጤና ሽፋን እንዲያድግ ታላላቅ ሆስፒታሎች ተሰርተው ለአገልግሎት መዋላቸውን መጥቀስም ግድ ይላል። ታላቁን ዘመናዊ የቀለበት መንገድ ግንባታ ጨምሮ የዋና ዋና እና የውስጥ

ለውስጥ አዳዲስ መንገዶች ስራ እና ጥገናዎች በስፋት በመሰራታቸው እነሆ የቀናት ጉዞ ወደ ሰዓታት ተቀይረው ህብረተሰቡ በቀላሉ ከቦታ ቦታ እንዲዘዋወር ምቹ ሁኔታ ፈጥሮለታል።

በአጠቃላይ የህብረተሰቡን መሰረታዊ ፍላጎት በማሟላት በኩል አመርቂ ስራዎች መሰራታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በኢንቨስትመንት በኩልም የዓለም የኢኮኖሚ ዋልታ ከሆኑት ቻይና እና ህንድ ጋር ከተጀመረው የንግድ እንቅስቃሴ በተጨማሪ  በተለይ በጅግራፊ አቀማመጣቸው ጎረቤታችን ከሆኑ እንደ ሳዑዲ አረቢያ ካሉ የመካከለኛው ምስራቅ ሃገሮች ጋር እየታየ ያለው የጋራ ልማት መልካም ጅምር እያስመዘገብን ላለው ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት መሰረት በመጣላቸው ሃገራችንን ወደ ተሻለ አዲስ የእድገት ምእራፍ እና መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሃገሮች ጋር በመሰለፍ በትክክለኛ መስመር ላይ እየተጓዘች ለመሆኑ ከእኛም አልፎ ሌሎች ሃገሮች እየመሰከሩት ያለው እውነታ ነው። ዓለም አቀፍ ደረጃውን ጠብቆ የተገነባው ሁሉን አቀፍ የቦሌ አውሮፕላን ማረፊያም የሃገራችንን ውብ ገጽታ እና የስኬታችን አመላካች መሆኑ ብሄራዊ ኩራታችን ነው።

በአሁኑ ወቅትም የህዳሴው ግድብ መጀመሩ የወደፊት ብሩህ ተስፋችንን አመላካች በመሆኑ ለመንግስታችን እና በአጠቃላይም ለኢትዮጵያ ህዝብ የተሰማንን ልባዊ ደስታ በዚህ አጋጣሚ መግለጽ እንወዳለን።

እነዚህ አኩሪ የልማት እንቅስቃሴዎች ዘላቂነት የሚኖራቸው የህብረተሰቡ መብት እና ሃይማኖታዊ እሴቱ ተከብሮለት አስተማማኝ እና ዘላቂ ሰላም ሲኖር ብቻ መሆኑን ለዘመናት በጠርነት ስትታመስ ለኖረች ሃገራችን እውነታው የተሰወረ አይደለም።

## <u>ክቡር ጠቅላይ ሚኒስቴር</u>

ሃገራችን ኢትዮጵያ ከ1435 አመት በፊት የነብዩ ሙሐመድ ተከታዮች በኢትዮጵያ ንጉስ ዘንድ ማንም ሰው ስለማይበደል አላህ የተሻለ ነገር እስኪያመጣላቸው ድረስ ወደ ሃበሻ ሄደው እንዲኖሩ  በነብያቸው አማካኝነት ሲላኩ በእንግዳ ተቀባይነቱ የሚታወቀው የኢትዮጵያ ህዝብ ስደተኞችን በመልካም ተቀብሎ በማስተናገድ እና የመንግስትን ጥበቃ እና ከለላ አግኝተው  ለብዙ አመታት በሰላም እና በክብር እንዲኖሩ በማድረጋችን የሃገራችን በጎ ገጽታ በየትኛውም የአለም ክፍል የሚኖሩ ሙስሊሞች ለዘለዓለም በመልካም የሚዘክሩት የአኩሪ ታሪክ ባለቤት አድርጎናል።

ዳሩ ግን 'የአባይን ልጅ ውሃ ጠማው' እንዲሉ ሙስሊሙ ህብረተሰብ ባለፉት ስርዓቶች መብቱ ሳይከበርለት ለብዙ ዘመናት ሲጎሳቀል መኖሩ ደግሞ ታሪክ የማይክደው እውነታ ነው።

የሥርዓቱ ገፈት ቀማሽ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ቢሆንም የሙስሊሞቹ ሁኔታ ግን በተለየ መልኩ  እጅግ የባሰ ነበር ቢባል ማጋነን አይሆንም። ለዘመናት ብሶት ያንገፈገፈው ህዝብ ከአብራኩ በወጡ ታጋይ ልጆቹ አፋኝ እና ጨቋኝ የነበሩ ስርዓቶችን ሁሉ ገርሥሶ ዲሞክራሲያዊ መንግስት ከተመሰረተ በኋላ የዜጎች መብት ይጠበቅ ዘንድ  በህገመንግስቱ ዋስትና በማግኘቱ እነሆ ስለ መብት መከበር ብቻ ሳይሆን አንድ እርምጃ ወደፊት ተጉዘን የተኩረት አቅጣጫችንን ወደ ልማት አዙረናል ብለን በምናምንበት ወቅት  እና ለህዳሴው ግድብ የጋራ እርብርብ በምናደርግበት ዋዜማ ላይ የልማት ጉዞአችንን የሚያስተጓጉል እና የሙስሊሙን ሰላም የሚነሳ  አንድነቱን የሚያናጋ እና በሃገሪቱም ላይ ለሃይማኖት መቻቻል እየጣልን ያለውን መሰረት

የሚፈታተን ሁኔታ መከሰቱን እየተከታተልን እንገኛለን። በመንግስት እና መጅሊስ ጥምረት አህባሽ በመባል የሚታወቀውን ጽንፈኛ እምነት በአርስ በአርስ ጦርነት በመተረማመስ ከምትታወቀው ሊባኖስ አስተማሪዎችን በማስመጣት እና ሰሚናር በማካሄድ በኢትዮጵያ ሙስሊሞች ላይ ይህን እምነት በግድ ለመጫን የሚደረጉ መጠነ-ሰፊ እንቅስቃሴዎችን በግርምት እና በትዝብ ማየት እና መስማት ከጀመርን ውለን አድረናል።

ለአህባሽ እምነት በጀት መድቦ እያካሄደ ያለው ሰሚናር ከተለያዩ ሙስሊም ወገኖች ተቃውሞ እየገጠመው በመምጣቱ ህብረተሰቡም ቅሬታውን በሰላም እያሰማ ባለበት ሁኔታ እንኳ ለህዝቡ አቤቱታ ትኩረት ሳይቸረው ሰላሳ ሺ.ህ የመስጅድ ኢማሞችን የሚያጠቃልል ተጨማሪ ስልጠና ለማድረግ መንግስት እና መጅሊስ በዝግጅት ላይ መሆናቸው አስገርሞናል።

ከሁሉ አስቀድሞ ሃገራችን ኢትዮጵያ የታላላቅ የኢስላም ምሁራን መፍለቂያ እና ባለቤት ሆና እያለ ከውጭ ሃገር አስተማሪ ማምጣት ያስፈለገበት ምክንያት ብዙ ነገሮችን በጥርጣሬ እንድንገምት አስገድዶናል። ከሌሎች እምነቶች ጋር ተቻችሎ መኖርን በማደፍረስ ለሊባኖስ አለመረጋጋት ከፍተኛ የ አራስ ምታት በመሆኑ በግልጽ እና በተግባር የሚታወቀው አህባሽ የኢትዮጵያ ሙስሊሞችን አንድነት የሚበታትን እና የሃገራችንን ሰላም የሚያደፈረስ በመሆኑ በመንግስት እና መጅሊስ ድጋፍ እየተሰጠ ያለውን ባዕድ አስተምህሮ በጽኑ እንቃወማለን።

ህገመንግስታችን የህዝቦችን የእምነት ነጻነት መብት ከመጠበቅ ባሻገር ሃይማኖት በመንግስት ጉዳይ እንደማይገባ ሁሉ መንግስትም በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ እንደማይገባ በማያሻማ መልኩ ደንግጎ አስቀምጦታል። ይሁን እንጅ በህገመንግስቱ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 3 ከተደነገገው መርህ ጋር ጭራሽ ሊጣጣም በማይችል መልኩ በሙስሊሙ እምነት ውስጥ ጣልቃ በመግባት የህገመንግስት ጥሰት በግልጽ እየተስተዋለ፣ያለበት ሁኔታ በሙስሊሙ መካከል ብዥታን ፈጥሯል።

በመሆኑም ከዚህ በታች የተጠቀሱትን አንገብጋቢ የሙስሊሙ ህብረተሰብ ችግሮች ለክቡርነትዎ ስናቀርብ መፍትሄ እንደምናገኝም በመተማመን ነው።

1ኛ/መንግስት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ለአህባሽ የሚሰጠውን ድጋፍ እንዲያቆም እና በሌሎች የ እምነት ተቋሞች ላይ በፍጹም ጣልቃ እንደማይገባ ሁሉ በሙስሊሙ ህብረተሰብ ላይ ያለውን ጣልቃ ገብነት እንዲያነሳ እንጠይቃለን።

2ኛ/ሌሎች የእምነት ተከታዮች በጠቅላላ የሃገሪቱ ክፍል በታላላቅ ዩኒቨርስቲዎች ሳይቀር ሃይማኖታቸውን የመስበክ እና የማስፋፋት መብት ያለገደብ ሲኖራቸው ሙስሊሞቹ ግን እምነታቸውን በነጻ እንዳይተገብሩ እና ወገኖቻቸውን እንዳያስተምሩ በዳዕዋ እንቅስቃሴ ላይ በመጅሊስም ይሁን በመንግስት እየተደረገ ያለውን ማዕቀብ እና ማሳደድ በጽኑ እንቃወማለን።

3ኛ/በተለያየ ጊዜ እና አጋጣሚ በትምህርት ተቋማት በሙስሊም ተማሪዎች ላይ በሰላት እና በሂጃብ ዙሪያ የሚደረጉ ትንኮሳዎችን እና በዚሁ ሰበብ ሙስሊም ተማሪዎችን የማሸበር እና ከትምህርት ገበታቸው የማፈናቀል የተጠናከረ ዘመቻ ከጊዜ ወደ ጊዜ እጅግ በጣም እየበዛ በመምጣቱ ሙስሊሙ ህብረተሰብም የልብ ትርታውን እና ህመሙን የሚያዳምጥለት አካል በማጣቱ አዝኗል። በተለይ በ2004 እንደሚተገበር

የተነገረለት እና በሙስሊሞች ላይ ብቻ ያነጣጠረውን ሰላትን በጋራ እንዳይሰገድ እና ሂጃብ እንዳይለበስ የሚከለክል የትምህርት ሚኒስትር መመሪያ ከጅምሩ በጽኑ የተቃወምነው ከመሆኑም ባሻገር ከእስልምና ህግጋት ጋር የሚቃረን በመሆኑ በፍጹም እንደማንቀበለው እንገልጻለን።

ይህ መመሪያ በህገመንግስቱ በግልጽ የሰፈረውን የግለሰቦች በግልም ይሁን በጋራ የአምልኮ መብት የሚጋፋ ከመሆኑም በተጨማሪ ፣በሙስሊሞች ህልውና ላይ በተደጋጋሚ እየደረሰ ካለው የቁርዓን መቃጠል እና የመስጊዶች ማፍረስ ዘመቻ ጋር በተያያዘ ስውር እጅ እና ጥቅም ያላቸው ወገኖች መንግስትን እና ስልጣናቸውን ሽፋን በማድረግ የሚሰሩት ደባ እና የሚያስፈጽሙት ስውር አጀንዳ በመሆኑ ይህ ጉዳይ በአስቸኳይ እልባት እንዲሰጠው እያሳሰብን ሰላትን በጋራ መስገድ እና ሂጃብ መልበስ የእምነታችን አካል መሆኑን በድጋሚ እየገለጽን የማያሻማ ህግ ወጥቶለት ሙስሊሞች ሳይሸማቀቁ እምነታቸውን ይተገብሩ ዘንድ መመሪያ ለሁሉም አካላት በተዋረድ እንዲተላለፍ ሆኖ በየጊዜው በሰላት እና ሂጃብ ዙሪያ የሚከሰቱ ችግሮች እልባት እንዲያገኙ በአጽንኦት እንጠይቃለን። ለወደፊቱም ሙስሊሞች እና እምነታቸውን የሚመለከት ህግ ማርቀቅ ሲታሰብ የጉዳዩ ባለቤት የሆኑት ሙስሊም ምሁራን ተሳትፎ እና አስተያየት ያማከለ መሆን እንዳለበት እንጠቁማለን።

4ኛ/ ህዝበ ሙስሊሙ ያልወከላቸው እና በሙስና የተዘፈቁ እንዲሁም ሙስሊሙንም ለመምራት ሃይማኖታዊ ብቃት የሌላቸው የመጅሊስ መሪዎች ሃላፊነታቸውን በመዘንጋት እና ለአህባሽ በመወገን አንድነታችንን በመበታተን ሌሎች ሙስሊሞች ሃይማኖታዊ ትምህርት እንዳይሰጡ በመከልከል በኢስላም እና ሙስሊሞች ላይ እያደረሱ ያለው በደል ከጊዜ ወደጊዜ በመበራከቱ ትከሻችን ለመሸከም ከማይችለው ደረጃ ላይ ደርሷል። ይህ ደግሞ በሃገሪቱ ሁለንተናዊ ሰላም እና ልማት ላይ ችግር እና አለመረጋጋት እንደሚፈጥር ታውቆ ሙስሊሙ ያገለግሉኛል ያላቸውን ሰዎች ይመርጥ ዘንድ በተደጋጋሚ የቀረበው አቤቱታችን ሰሚ ጆሮ ያገኝ ዘንድ በአንክሮ እንጠይቃለን።

5ኛ/ የእስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ጉባኤ በመባል የሚታወቀው የሙስሊሞች ብቸኛ ተቋም እንደ ተራ የበጎ አድራጎት ድርጅት ፈቃዱ በየዓመቱ መታደሱ አግባብ እንዳልሆነ በበድር ዓለም አቀፍ የሙስሊሞች ተወካይ አማካኝነት ቅሬታችንን በመግለጽ እንደ ሌሎች እምነቶች ህጋዊነቱ በአዋጅ ይጸድቅ ዘንድ ብንጠይቅም እስከአሁን ተፈጻሚ ባለመሆኑ ጉዳዩ ይስተካከል ዘንድ አሁንም በድጋሚ እንጠይቃለን።

6ኛ/ የዲሞክራሲ ጸሃይ እንዳሁኑ አክሱም ባሉት ሙስሊሞች ላይ ሳትደበዝዝ ኢትዮጵያችን እንኳንስ ለዜጎቿ ይቅርና በእምነታቸው ምክንያት የእኛን ከለላ በመፈለግ ለተሰደዱት ሙስሊሞች እንኳ ከመጠጊያነት አልፈን በሃገራቸው ያላገኙትን የእምነት ነጻነት በኢትዮጵያ ያለምንም ገደብ እንዲተገብሩ የመደረጉን ወርቃማ የታሪክ ብርሃን ለአለም ህዝብ እየተንጸባረቀ እና ኢትዮጵያውያን ለኢስላም የዋሉት ውለታ የትምህርታቸው አንዱ ክፍል ሆኖ ለትውልድ እየተላለፈ ባለበት ሁኔታ የአክሱም ሙስሊሞች በአምልኮት ነጻነት ዙሪያ ህግ ህገመንግስቱ ያጎናጸፋቸውን መብት እንዳይጠቀሙ የመሆናቸው ሚስጥር ሙስሊሙ የህይወት ዘመኑ እንቆቅልሽ ሆኖበታል። ለሃገራቸው ዳርድንበር መከበር አጥንታቸውን መከስከሳቸው እና ደማቸውን ማፍሰሳቸው ተዘንግቶ በሃገራቸው ባይታወር መሆናቸው ያከትም ዘንድ በተደጋጋሚ ጥያቄ ቢቀርብም መንግስት በዚህ ጉዳይ ላይ እንደ ሃገር መሪነቱ ሃላፊነቱን ባለመወጣቱ ከታሪክ ተወቃሽነት አያመልጥም። በተጨባጭም ጥያቄውን ለመመለስ እየወሰደው ያለው እርምጃ ባለመኖሩ ግርምታችንን ጨምሮታል። የአክሱም ሙስሊሞች ጉዳይ የዘመናት የኢቶዮጵያ ሙስሊሞችን

የጭቆና ታሪክ በዛሬ መስታወት የምናይበት አስገራሚ መድረክ ሆኖ መቀጠሉ ትውልድ የማይረሳው ጠባሳ ጥሎ እንዳያልፍ እንሰጋለን። በመሆኑም የአክሱም ጉዳይ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች የማንነት ጉዳይ መሆኑ ተሰምሮበት እንደሙብት እና እንደዜጋ መስጊድ የሚገነቡበት ቦታ ይሰጣቸው ዘንድ በአንክሮ በድጋሚ እንጠይቃለን።

7ኛ/ የሃገሪቱ የፖለቲካ ሁኔታ ያለመረጋጋት አዝማሚያ በታየበት ወቅት ሙስሊሙ ከመንግስት ጎን በመቆም ሰላም ወዳድነቱን እና የመንግስት ሁለንተናዊ ሚዛን እንዲጠበቅ ድምጹን ከመስጠት አልፎ ለአፍራሽ ጥሪ ጆሮ ሳይሰጥ ለህገመንግስቱ ያለውን ክብር እና ታማኝነት ከአንዴም በላይ ለማሳየቱ መንግስት በራሱ ምስክር ነው። የሃይማኖት ሙብቴ ይከበርልኝ በማለት ሰላማዊ ድምጹን የሚያሰማውን ሙስሊም ወገን ለሃገር ሉአላዊነት እና ደህንነት አስጊ አድርጎ በመሳል ወሃብይ እንዲሁም አሽባሪ እና አክራሪ ብሎ መፈረጅ ኢትዮጵያዊ ባህል እንዳልሆነ እየታወቀ እንደ ምሳሌ እንኳ የሚጠቀስ በሙስሊሞች የተፈጠረ አንድም የሽብር ተግባር በሃገራችን ባልተከሰተበት ሁኔታ ሰላማዊውን ሙስሊም ማደናገጥ እና ማስፈራራት ፖለቲካዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው አይታየንም። የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ከጥንት ጀምሮ የነብዩ ሙሃመድን ትክክለኛ አስተምህሮ የሚከተሉ እና የ4ቱ መዝሀብ ተከታዮች በመሆናቸው በመቻቻል እና በመከባበር የሚያምኑ ሰላማዊ እና ሚዛናዊነታቸውን በሙሉ ልብ እያረጋገጥን ወሃብይ በመባል የሚታወቅ እምነትም ፍጹም እንደሌለ እናረጋግጣለን።

በመሆኑም በሰላማዊ መልኩ ሙብቱን ለማስከበር የሚታገለውን ሙስሊም አክራሪ እና አሸባሪ እያሉ መፈረጅ እና ማስፈራራት ብሎም ለእስራት መዳረግ ሰላምን እንደሚያደፈርስ እና ከልማትም እንደሚያስተጓጉል ታውቆ ለሌላ እምነት ተከታይ ያልተሰጠ የአክራሪነት እና አሸባሪነት ስም ከሙስሊሙ ላይ እንዲነሳ እና ከመጅሊስ ጋር በመቀናጀት የሚደረግ ማንኛውም አይነት ማስፈራራት እና እስራት እንዲቆም እንጠይቃለን።

በመጨረሻም የኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ችግር እንደ አኩሪ ቅርስ እና ታሪክ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍበት ምዕራፍ ያበቃ ዘንድ በድር አለም አቀፍ የሙስሊሞች ፌዴሬሽን ከአሁን በፊት ያቀረባቸው እና ምንም አይነት ምላሽ ያላገኙ ጥያቄዎች መልስ እንዲያገኙ በድጋሚ እየጠየቅን በሳኡዲ አረቢያ ጅዳ ጣኢፍ መካ እና መዲና የሚኖሩ ሙስሊሞች እርስዎን የሚያናግር ልዑካን ለመላክ ዝግጁ በመሆናቸው እድሉ ይሰጣቸው ዘንድ ይሁንታዎን በትህትና እንጠይቃለን።

ከሰላምታ ጋር

በጅዳ ጣኢፍ መካ እና መዲና የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች

<u>ግልባጭ</u>

ለኢትዮጵያ ቆንስላ ጽ/ቤት ጅዳ ሳኡዲ አረቢያ